# ዴሞክራሲያ

*******************************************************

* የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ዴሞክራሲያዊ) ልሣን*

*******************************************************

ቅጽ 40 ልዩ ዕትም ግንቦት 2006


## በሀገር ዳር ድንበር አንደራደርም!

ኢትዮጵያውያን የምንኮራበት የሀገር ባለቤትነትና የዜግነት መታወቂያችን ያለአንዳች ጥርጣሬ ከሀገራችን ከኢትዮጵያ ሕልውና ጋር የተሳሠረ መሆኑን በፍጹም አንስተውም። ይህ ደግሞ ማንነትን ማወቅ ነው፤ ኢትዮጵያ የእኛ ናት፤ እኛም የእሷ ነን። እስከዛሬ በረዥሙ ታሪካችን ውስጥ ዕልፍ አዕላፍ ሕይወት ስንከፍል የኖርነውም፣ ሀገራችን በነፃነቷ ታፍራና ተከብራ እንድትኖር ነው! ወደፊትም ለዚሁ ዓላማ ሁኔታዎች የሚጠይቁትን አስፈላጊውን መስዋዕትነት ሁሉ ምንጊዜም ያለማመንታት ለመክፈል ዝግጁነታችን እናረጋግጣለን።

"እያ ጅቦ ሳታመኻኝ ብላኝ!" የሚለው የአባቶቻችንና የእናቶቻችን አባባል ብልኅነትን፣ ብስለትንና አርቆ አስተዋይነትን ገላጭ እንጂ ተራ ብልጣብልጥነትን የሚያሳይ አይደለም። ኢትዮጵያውያንን እንደሕዝብ ማታለል በጣም ከባድ፣ ምናልባትም የማይቻል ነገር ነው ቢባል ስህተት አይሆንም። በቀድሞ ዘመናትም ባዕዳን ሞክረው አልቻሉም። የኢትዮጵያ ሕዝብ ማንነት ከረዥም ታሪኩ ጋር የተሳሰረ በዚያም ላይ ተመሥርቶ እየበለጸገ የመጣ ስለሆነ፣ የዛሬዎቹ ገዥዎቻችን ይህንን ለማፍረስ እንዲያመቻቸው ታሪካችንን ሊያንኳስሱ ቢሞክሩም፣ ከነሱ ይበልጥ ስለማንነታችን ስለምናውቅ፣ አትቅጠፉ እኛ በርግጥም የረዥም ታሪክ ባለቤቶች ነን እንላቸዋለን። የብልህነታችንን አሻራ የያዘው ረዥሙ ታሪካችን ነውና! ቋንቋዎቻችንን፣ ባህሎቻችንን፣ የጋራ ታሪካችንን በጽሞና ከመረመርን በጣም ብዙ ጠቃሚ ትምህርት ልንቀስምባቸው እንችላለን። የበርካታ አባባሎችንን ውስጠ-ወይራነትን ማጤንም ጠቃሚ ይሆናል። ንግግራችን ሁሉ ሰምና ወርቅ የተላበሰ በመሆኑም ነው ሰሙን አቅልጠን ወርቁን የምናገኘው!

ሱዳን ባለፉት 25 እና 30 ዓመታት ውስጥ ኢትዮጵያ የገባችበትን አዘቅት ስላወቀች ያገኘችውን አጋጣሚ ሁሉ ተጠቅማ በኢትዮጵያ ላይ ስትራተጂያዊ ጉዳት እያደረሰች ነው። ሱዳን የህወሓት መሪዎችን ባስፈለጋቸው ሁሉ እገዛ አድርጋ ኢትዮጵያ ውስጥ በትረ-መንግሥቱን ካስጨበጠችበት ወቅት ጀምሮ አንዳችም ችግር ሳይገጥማት ትመኘው የነበረውን የኢትዮጵያን ለም፣ ደን-ለበስና ወኃ-ገብ ሰፊ ድንበራችንን እየወሰደች ነው! የጅብን ያህል እንኳን "ሳታሳብብ" ቅርጥፍጥፍ አድርጋ እየበላችን ነው። የሕዝቡ የሀገራዊ አንድነትና አትንኩኝ ባይነት ስሜት በፀረ-አንድነቱና ፀረ-ኢትዮጵያው ህወሓት በከፍተኛ ደረጃ ከተቦረቦረና ከተዳከመ በኋላ ሰተት ብላ ገብታ ቀድሞ በትግል ላይ እያሉ ከዛሬዎቹ መሪዎች፣ ምናልባትም ከከፊሉ፣ ከመለስና የቅርብ ተከታዮች ጋር ያሴረችውን ማለትም ያስገባቻቸውን ቃል-ኪዳን ዛሬ በተግባር እንዲፈጽሙላት እያደረገች ነው። ኤርትራ እንድትገነጠል፣ በተጓዳኝም በተለይ ህወሓት በኢትዮጵያ የፖለቲካ ሥልጣን እንዲጨብጥ ለማስቻል ሱዳን በልዩ ልዩ መልኩ ያላደረገችው ጥረት አልነበረም! በመጨረሻ በወታደራዊ ርብርባቸው ወቅት በየምሽቱ ከአርባ እስከ ሃምሳ የሚደርሱ የጭነት መኪናዎች በየሌሊቱ ወሰን አቋርጠው ለህወሓትና ለሻዕቢያ ኃይሎች ስንቅና ትጥቅ ያቀብሉ ነበር። ሲመለሱም የተዘረፉ ንብረቶችን ይዘው ነበር ይወጡ የነበሩት። ሻዕቢያ "ዐረብ ነንና የዐረብ ሊግን እንቀላቀላለን!" እያለ ያማልል ነበር። ህወሓት ግን አንዴ መለስ ስለየመናዊ ዝሪያው ለቃዳፊ ከዋሸው ሌላ ስለዐረብነታቸው ብዙም አልተናገረም፤ ታዲያ ለምን ከዚህ ቡድን ጋር ሱዳን ልዩ ትብብር አደረገች?

ማንኛውም ሕዝብ ሀገሩ መኖሪያው፣ መታወቂያው፣ እንዲሁም መጠቀሚያውም ነውና ሀገሩን ከወራሪ፣ ከተስፋፊና ከቅኝ-ገዥ መከላከል ይጠበቅበታል። ሕዝብ የሀገሩ ባለቤት ነው። ለሀገሩ ደሙን ያፈሰሰ ወይም ሊያፈስ ዝግጁነት ያለው ዜጋ ከሁሉም የሀገሩ አንጡራ ሀብትና ንብረት የድርሻውን ማግኘት ይገባዋል፤ ከሚገባው በላይ ደግሞ ሊሰጠው አይገባም። ባይለማም ወይም ድኃ ቢሆንም፣ ሀገር ለዜጎቿ ንዑድና ክቡር ናት። ኢትዮጵያ እኮ ደሀ ናት፤ ምን አላትና ነው የምንኩራራባት የሚሉ ካሉ ተሳስተዋል። ኢትዮጵያችን ነፃነቱን በከባድ መስዋዕትነት አስከብሮ የሚኖር ኩሩ፣ ታታሪ ሠራተኛ፣ ብልኅና አስተዋይ ሕዝብ የሚኖርባት እንዲሁም ሊለማና ሊያመርት የሚችል ሰፊና ለም መሬት ያላት አገር ናት። ይህ ብቻም አይደለም፤ ማራኪ የሆነ መልከዓ-ምድር ያላት፣ ቆላ፣ ወይናደጋና ደጋ የአየር ጠባይ ያላት ፣ ብርቅዬ አዕዋፍት፣ እንስሳት፣ ዕፅዋትና አዝርዕት የሚገኙባት፣ አልፎ ተርፎም ከራሷ ለም አፈር አዝለው የሚዞሩ ወንዞችንና

ጅረቶችን፣ ሐይቆችንና ኩሬዎችን፣ ከመሬት ሥር የተኛ ወኃን ጭምር ተፈጥሮ ያደላት ሀገር ነች። የውኃ ሀብት በጥቅም ላይ ከዋለ፣ ሀገራችንን ከረሀብና ችግር ሊያላቅቃት የሚችል፣ ወደፊት ደግሞ ይበልጥ ውድ እየሆነ የሚመጣ፣ ከውድ ማዕድናት የማይተናነስ፣ ትልቅ የሀገር የተፈጥሮ ሀብት ነው። ይህ ሁሉ የተፈጥሮ ፀጋ ተደማምሮ አገራችንን ኢትዮጵያን በዋጋ የማትተመን ንዑድ አገር አድርጓታል።

ኢትዮጵያ በተፈጥሮ የያዘችው ሥፍራና ጂኦግራፊያዊ አቀማመጧም በርካታ ታሪካዊ ትስስሮችን ፈጥሮላታል። የሰው ልጅ ምንጭነት፣ የዓለም ረዥሙ ወንዝ የዓባይ ምንጭ ባለቤትነት፣ የዐረቦችና የጥቁር አፍሪካውያን መገናኛና መቀላቀያነት፣ የበርካታ ቋንቋዎችና ባህሎች እንዲሁም ለታላላቅ ሃይማኖቶች መተሳሰሪያነት አንድ ታሪካዊ መተላለፊያና መሸጋገሪያ በሆነ አካባቢ ከመቀመጧ የተገኙ እሴቶች ለማንነቷ ከፍተኛ አስተዋፅኦ አድርገዋል።

የቀይ ባህር ወደቦች ባለቤት በመሆኗም፣ ያኔ፣ የመካከለኛው ምሥራቅ ችግር ተካፋይ ሆና ኖራለች። ከእስራኤል ጋር በመወዳጀቷና በዓባይ ወንዝ ምንጭነቷ የተነሳም የዐረብ ሀገሮች በተለይም ግብፅ፣ ሶሪያ፣ ኢራቅ፣ ሊቢያ…ወዘተ ሊወሯት፣ ሊቆጣጠሯት፣ ሊከፋፍሏትም ሲጥሩና የውክልና ጦርነት ሰለባ ሲያደርጓት ኖረዋል፤ ዛሬም ቢሆን መዘዙ ከቶውንም ተባባሰ እንጂ አልጠፋም። በመጨረሻም ኤርትራን አስገንጥለው “ዐረባዊነት” ቡልኮ አልብሰው፣ መሣሪያቸው በማድረግ አሁን ላለንበት ሁኔታ ያለጥርጥር ትልቅ ድርሻ አበርክተዋል። እስራኤልና አጋሯ አሜሪካ ደግሞ ለረጅም ጊዜ ኢትዮጵያን የራሳቸው ተባባሪና መሣሪያቸው ሊያደርጓት ሞክረዋል። በመጨረሻም በሚስጥራዊ ድርድር ኤርትራን ከእስራኤል ጋር ለማወዳጀት ቅድመ-ስምምነት ላይ ስለደረሱ አሜሪካና እስራኤል የኤርትራን መገንጠል በመደገፍ የህወሓትንና የዐረቦችን ትልም ተግባራዊ በማድረግ ወሳኝ ሚና ተጫውተዋል። በለንደን የተካሄደው ሤራ አሜሪካና እንግሊዞች ከገንጣዮች ጋር መመሳጠር የተከናወነ ነው።

ከግብፅና ከሱዳን ጋር ያለን ችግር የቆየ ነው። የኦቶማን ቱርኮች ተወካይ በመሆን “የቱርኮ-ኢጂፕሽያን” አስተዳዳሪ የነበረው ከዲቭ ኢስማኤል የዓባይን ሸለቆ በሙሉ ለመያዝ በማሰብ፣ በመጀመሪያ ስትራተጂያዊ የሆኑትን የቀይ ባህር ወደብ አካባቢዎችን ለመቆጣጠርና ኢትዮጵያን ለማፈን በአውሮፓውያኑ አቆጣጠር በ1872 ምፅዋን በመውረር ከግዛቱ ከሱዳን ጋር አዋህዶ ለመግዛት ሞክሮ ነበር። በዚያ በኩል አልሳካለት ሲልም፣

በበርበራ በኩል ሐረርንም አብሮ ለመያዝ ሞክሯል። ከዲቭ ኢስማኤል በሰሜናዊቷ ክፍለ ሀገራችን በኤርትራ በኩል በኅዳር 1875 ዓ. ም በጉንደት ለጥቆም፣ በመጋቢት 1876 ዓ. ም በጉራዓ ወረራ አድርጎ በራስ አሉላ አባነጋ የጦር መሪነት በኢትዮጵያዊያን አሸናፊነት ዓላማው ተደናቅፎበታል። ስለዚህም ከዲቭ እስማኤል ኢትዮጵያን ወሮ ለመያዝ አልተቻለውም። ልጁን ተውፊቅ እስማኤልን አሻንጉሊቷ አድርጋ ከ1879 እስከ 1884 ግብፅንና ሱዳንን በእጅ አዙር፣ ዩጋንዳንና ታንዛኒያን ደግሞ በቀጥታ፣ በቅኝ ግዛትነት በመያዝ፣ አካባቢውን ለመቆጣጠር የቻለችው አመርቃኘ-ቁስል የመፍጠር ልማድ ያላት እንግሊዝ፣ ኢትዮጵያንም በቀጥታ ወርራ ለመያዝ ባትችልም፣ ጉዌን በሚባል አንድ የጦር መኮንኗ አማካይነት የኢትዮጵያ ተወካይ በሌለበት በትዕቢት ተወጥራ በቅኝ ግዛት ለያዘቻቸው ለግብፅና ለሱዳን የሚያዳላ፣ እሷ ራሷ የወሰን መስመር ያለችውን፣ በኢትዮጵያና በሱዳን ድንበር አካባቢ ችካል በማስቸከሏ ይኸውና ለዛሬም ለነገም የሚሆን ችግር ተክላብናለች።

በዓለም ረዥሙ የሆነው የዓባይ ወንዝ፣ ከዘጠኝ ያላነሰ በአፍሪካ አህጉር የሚገኙ ሀገሮችን በተፋሳሽነት ያገናኛል፤ መሬቶችን በተፈጥሯዊ ውበት ከማስተሳሰር ባሻገር ውኃውን ያቋድሳል፤ በይበልጥ እንዲጠቀሙበትም ያጓጓቸዋል። እያንዳንዱ ሀገርም እንደ አቅሙ ገፋ አድርጎ ለመውሰድ በከጀለ ቁጥር ሀገሮችንና ሕዝቦችን ሲያጋጫቸው ይታያል። ይህ ጉዳይ በዘዴ ካልተያዘም የዓባይ ተፋሳሽ ሀገሮችን ሕዝቦች ሕይወት ከክረምቱ ጎርፍ በባሰ ደረጃ ሊያደፈርሰው ይችላል።

ዊኪ-ሊክስ ስለ ሆስኒ ሙባረክ ከሰጠው መረጃ እንደምንረዳው፣ የግብፅ ገዥዎች በየተራቸው በዓባይ ውኃ እነሱ እንደልባቸው እንዲጠቀሙበት እንጂ ሌሎቹ የዓባይ ተፋሰስ ሀገሮች ሊገድቡ ቢሞክሩ ግድባቸውን በዓየር ደብድቦ እስከማፍረስ ድረስ ሲዝቱና ሲያቅዱም ኖረዋል። ከሙባረክ መውደቅ በኋላም መሐመድ ሙርሲ እንደ ኢትዮጵያ ያሉ ሀገሮች ዓባይን ቢገድቡ እስከ ጦርነት ለመሄድ ዝቶ እንደነበር የሚታወስ ነው። ከሌሎች የግብፅ ፖለቲከኞች አፈትልኮ ከወጣው የቴሌቪዥን ውይይት እንደተረዳነውም፣ ኢትዮጵያ ዓባይን ለመገደብ ብትሞክር፣ ጠባብ ብሔረተኛ ድርጅቶችን በመርዳትና በኢትዮጵያ ዙሪያ ያሉትን ኃይላትንም በፀረ-ኢትዮጵያ እንቅስቃሴ ላይ በማሰማራት ሀገሪቱን ለማበጣበጥ ጭምር እንደሚሠሩ ተጠቁሟልና ይጠበቃል። እንደማይተኙልን በርግጠኛነት መናገር ይቻላል።

ዓረባዊ ባህል፣ ቋንቋና፣ ሥነ-ልቦና ስላለው ዐረብ ነኝ የሚለው፣ በዘር ምንጩና ገጽታው ግን አፍሪካዊነቱ የሚያመዝነው የሰሜን ሱዳን ሕዝብ፣ ከሌላኛው በተመሳሰይ መንገድ ከተለያዩ አፍሪካዊ ጎሣዎች ወደ ዐረብነት እየተለወጠ ከመጣው ከሀገረ-ምስር (ከዛሬዋ የግብፅ) ሕዝብ ጋር በጣም ብዙ ጠንካራና፣ የማይበጠሱ ትስስሮች አሉት። የግብፅና የሰሜን ሱዳን ሕዝቦች ብሔራዊ ቋንቋቸው ዐረብኛ ነው። የሥነ-ፅሑፍ፣ የዘፈን፣ የባህል፣ የሃይማኖት፣ የታሪክ እንዲሁም በዓባይ ውኃ ይበልጥ የመጠቀም ፍላጎትና ዓላማ፣ ከቻሉም ሁለቱ ብቻቸውን የሚጠቀሙበትን ሁኔታ ተጋግዞ የማቆየት ፍላጎትም ያስተሳስራቸዋል። በተለያዩ ታሪካዊ ሁኔታዎች ጠንካራ ትስስርና መተጋገዝ ሲያደርጉም ኖረዋል። የወደፊት መሪዎቻቸውንና የጦር መኮንኖቻቸውንም በጋራ የስትራቴጂ ተቋማትና ማዕከላት ሲያስተምሩና ሲያሰለጥኑ፣ ሲያለማምዱም ነው የኖሩት። የፖለቲካ ድርጅቶችም አንደኛው በሌላው ሀገር ውስጥ ቅርንጫፎች ወይንም ደጋፊዎች አሏቸው። የመካከለኛው ምሥራቅና የአፍሪካ ፖሊሲዎቻቸውን ተጋግዘውና አቀናጅተው ሲሠሩ የኖሩ ሁለት ወንድማማች የሆኑ ሀገሮች መሆናቸውንም ከቶውንም ልንዘነጋው አይገባም። እነዚህ መንግሥታት ኢትዮጵያን ለመጉዳት እስከዛሬ ድረስ ተጋግዘው በመሥራት ላይ ናቸው። ግብፅ ደቡቡ ሱዳን እንዳይገነጠል በማድረግ የሱዳን ሀገራዊ አንድነት ተጠብቆ እንዲኖር እየጣረች፣ ኢትዮጵያን ለመገነጣጠል ግን ግብፅና ሱዳን ያለማሰለስ ጥረው ይኸው ዛሬ ኢትዮጵያን ወደብ አልባ ከማድረግ አልፈው አዲስ አበባ ላይ ተባባሪቸው የሆነውን ቡድን ለሥልጣን አብቅተዋል። ስለሆነም ያለምክንያት አልነበረም ሱዳን ህወሓትን ከመርዳት አልፋ በዓላማ ከህወሓት የሚለዩትን፣ የህወሓትን ፖሊሲዎችና ተግባሮቹንም ሊቃወሙት የሚችሉ ኢትዮጵያዊ የአንድነት ኃይሎችን በጦርነት ለመደምሰስ አብራ ተቀናጅታ የሠራችው።

ከምናውቀው እንኳን ብንነሳ፣ የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኅብረት (ኢዴኅ) ከተመሠረተበት ጊዜ ጀምሮ ኢትዮጵያዊነትንና የሀገር አንድነትን በዓላማነት ያነገበ ኃይል ነበር። ታጋዮቹ ያለጥርጥር ሀገር-ወዳዶች ነበሩ። ሱዳንና ሌሎችም ኢትዮጵያን ማዳከም የሚፈልጉ ኃይሎች የኢትዮጵያውያን የአንድነት ኃይሎች መከፋፈል፣ እርስበርስ ማቃቃር፣ ማበጣበጥ፣ ከቻሉም ማጋጨትና ማዋጋት የመጀመሪያው ስልታቸው አድርገውት ነው የኖሩት። በተለያዩ በአመዛኙ ውስጣዊ ምክንያቶች ኢዴኅ ከተዳከመበት ወቅት ጀምሮ ሱዳን የኢዴኅ አባላትን ስደተኞች አድርጋ በየስደተኛ ጣቢያዎች በማስፈር ለዓመታት መንፈሳቸው እንዲላሽቅ አድርጋለች። በመጨረሻም ኢሕአፓን መምቻ ልታደርጋቸው ወሰነችና ይህንንም ተግባራዊ አድርጋለች።

ከ1976 ዓ. ም በኋላ ኢ.ሕአፓ ጭልጋ አውራጃን፣ በተለይም ቋራን፣ ማጠቢያን፣ ሰራቆን፣ ጋዝጌን ...ወዘተ መወንጨፊያዎቹ አድርጎ ለመስፋፋትና ለመጠናከር ችሎ እንደነበር አይዘነጋም። ወደጎጃም ዘልቆም ባህርዳርን፣ አገው-ምድርን፣ ለጥቆም ሙሉውን የመተክል አውራጃን አጠቃሎ በመያዝ መንነቀሳቀሻው አድርጎ ነበር። ሱዳን ኢ.ሕአፓን በተለያዩ ፀረ-ኢትዮጵያ ዓላማዎቹ ሊተባበር ይችል እንደሆነ ከአንዴም ሁለት ሦስት ጊዜ በተጨባጭ ሞክራ ነበር። ለምሳሌ፣ በመጀመሪያ የዓባይን ድልድይ እንዲያፈርስ በምክትል ጠቅላይ ሚንስትሩ በጀኔራል ዑመር አልጠይብ አማካይነት ተጠይቆ ነበር። ለዚህ ኢ.ሕአፓ በቀጥታ እንዲህ ያለ ተግባር አልፈጽምም በማለት ግልጽ አቋሙን አሳየ። ሁለተኛ ሳም ሰባት የሚባል መሣሪያ ሰጥታው የኢትዮጵያን የሕዝብ መጓጓዣ አውሮፕላንም ቢሆን መትታችሁ ጣሉ የሚል ሃሳብ ሰንዝራለት ነበር። አሁንም እንደገና ኢ.ሕአፓ ይህንንም አናደርግም የሚል መልስ ሰጠ። ለሦስተኛ ጊዜ ይባስ ብሎ የኢትዮጵያን የወሰን አካባቢ ለም፣ ውኃ-ገብ፣ ደን-ለበስ መሬት ሱዳን በዜጎቿ ማሳረስ ስትጀምር ኢ.ሕአፓ ዝም ብሎ ይመለከት እንደሆነ ለመፈተን ሞከረች። በማጠቢያ ወረዳ በኩል መርርትራድ፣ ሽኩሪያ...ወ.ዘ.ተ በሚባል የሽንፋ ወንዝ ዳርቻዎችን አካባቢም ቀድሞ ኢትዮጵያውያን ይጠቀሙባቸው በነበሩ ሥፍራዎች ሱዳናውያን ሃብታሞች በትራክተር እንዲያርሱ አደረገች። መሬቱ የኢትዮጵያ በመሆኑ ኢ.ሕአፓ ይህን ሁኔታ ሊቀበለው አልቻለም። ኢ.ሕአፓ ከአካባቢው ሕዝብ ጋር በመምከር ልዩ ሥልጠና ሰጥቶ አንድ ታጣቂ ቡድን በማቋቋም፣ መጀመሪያ ማረስ በጀመሩት የሱዳን ሀብታም አሳራሾች (ገበሬዎች) ላይ የማስለቀቅ እርምጃዎች ተወሰደ። ቀጥሎም የሱዳን መንግሥት ይባስ ብሎ የሱዳን ጠባቂ ወታደሮችን አምጥቶ በአካባቢው አሰፈረ። ኢ.ሕአፓም ወታደሮቹ ወራሪ ኃይል በመሆናቸው አስፈላጊ የሆኑ የማጥቃት ርምጃዎችን መውሰድ ጀመረ። በዚህን ጊዜ የሱዳን መንግሥት ኢ.ሕአፓን ቢያስፈራራም፣ ኢ.ሕአፓ ግን ከቶውንም አልተበገረም። እንዲያውም በጉዳዩ ላይ የፖለቲካ ግንዛቤም እንዲጠናከር በማድረግ ሰፋ ባለ አካባቢ ከጎጃም አዋሳኝ ወረዳዎች ጭምር ሕዝቡን በማስተባበር ጥያቄው የሕዝብ ጥያቄም መሆኑን ሱዳን እንዲያይና እንዲታቀብ፣ በወሰን ላይ ሕዝቡ ያውም ታጥቆ እንዲመጣና ጠንካራ አገር-ወዳድነት መንፈሱንም እንዲገልጽ በማድረግ፣ ሱዳንያውያኑ ቁርጠኛነታችንን እንዲረዱት አድርጓል። ሱዳን አሁንም ጥቃት የምትፈጽሙብኝ እናንተ ራሳችሁ ናችሁ ብላ ኢ.ሕአፓን በመክሰስ በወሰን አካባቢ በነበረ የኢ.ሕአሠ ኃይል ላይ ወታደራዊ ጥቃት ለማድረስ ሞከረች። የኢ.ሕአፓና የወታደራዊ ክንፉ የኢ.ሕአሠ አባላትም ከመከላከል አልፈው በሱዳኖቹ ላይ የበለጠ የሞት፣ የማቁሰልና የመማረክም ጉዳት አደርሱባቸው።

በዚህም የሱዳን መንግሥት ኢ.ሕአፓም ሆነ ሕዝቡ እንደማይበገሩለት በመረዳት ለጊዜውም ቢሆን ሰላም ለመፍጠር ተገዶ "እናንተም እኛም ባለንበት እንርጋ" ተባብለን፣ ሱዳን በዚያው በወትሮው ድንበሯ ላይ እንድትቆይ ተደርጎ ነበር። ሱዳን በወሰን አካባቢ የሚገኝ ማንኛውንም መሬት ለመያዝ ስትሞክር ኢ.ሕአፓ መሰናክል እንደሚፈጥርባትና እንደማይፈቅድላትም በተግባር አረጋግጧል።

በመጨረሻም፣ ኢ.ሕአፓና ሠራዊቱ ኢ.ሕአሠ በቀላሉ የማይበገሩ ሀገር-ወዳድና የአንድነት ኃይል መሆናቸውን ሱዳን በሚገባ ካረጋገጠች በኋላ፣ በሁለት ሌሎች መንገዶች ኢ.ሕአፓን ከነሠራዊቱ ለማጥፋት ተግታ መሥራት ጀመረች። ይህም አንደኛው ዘዴያቸው ኢ.ዴኅንና ኢ.ሕአፓን ማጋጨት ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ ከህወሓት ጋር ተባብሮ ኢ.ሕአፓን ከሱዳን አዋሳኝ ሥፍራዎች ማስለቀቅ፣ ከቻለም ማጥፋት ነበር። ለዓመታት በስደተኛ ካምፖች በብዙ እንግልት ያኖራቸውን የኢ.ዴኅ አባላትን አሰባስባ፣ አስታጥቃና አጓጉዛ ኢ.ሕአፓን "ከዚያ አካባቢ እንዲያባርሩ"፤ ለተወሰኑ የሱዳንን ተንኮል በበቂ ሁኔታ ላልተረዱ የኢ.ዴኅ አመራር አባላት መመሪያ ሰጥታ፣ ኢ.ሕአፓ ለተወሰኑ ዓመታት ማዕከሉ አድርጎ ሕዝቡንም አደራጅቶበት በኖረበት ቋራ ውስጥ አምጥታ አሰፈራቻቸው። ኢ.ሕአፓ የሱዳንን ተንኮል ለማክሸፍ ከኢ.ዴኅ አመራር ጋር በአፋጣኝ ልዑካን መድቦ ካርቱም ውስጥ በማነጋገር በሰላማዊ መንገድ ችግሩን ለመፍታት ከፍተኛ ጥረት አደረገ። የገቡትን የኢ.ዴኅ ታጋዮችን በማስተናገድ፣ በመርዳት፣ እንቅስቃሴዎቻቸውንም በማገዝ ጭምር ተባበረ። ጎን ለጎን ሊታገሉ እንደሚችሉ የሚያሠራ ወታደራዊ ምርጫንም አቀረበ። ከዚያም አልፎ ወደሚስፋፉበት ከኢ.ሕአፓ ሠራዊት ጋር አብረው ሊገቡ እንደሚችሉ ቃል ገባላቸው። ኢ.ሕአፓ በዚያን ወቅት በርግጥም ጠንካራና በሚገባ የተደራጀ ስለነበር፣ ኢ.ዴኅን እስከሚጠናከር በቋሚ መልክ ገንዘብ ለመደጎምም ዝግጁነቱን ገልጦላቸው ነበር።

በዚያን ጊዜ ኢ.ሕአፓ ወደ ጎጃም ተስፋፍቶ ሁለተኛ ማሠልጠኛውን በመተከል አውራጃ ወምበራ ወረዳ ውስጥ በማድረግ እየሠራ እያለ የተወሰኑ የኢ.ዴኅ መሪዎች ግን ተልዕኳቸው ሌላ ስለነበር፣ የኢ.ሕአፓን ጥረት አምክነው እጅግ አላስፈላጊና ጎጂም ወደሆነ የወንድማማቾች ውጊያ ውስጥ እንዲገባ ሆነ።

ሱዳን የኢትዮጵያን ድንበር ከመጋፋት አልፋ ሰፊ ክልል ለመያዝ ስትዘጋጅና ስትሠራ ኖራለች። ለዚህም በወሰን አካባቢ የሚኖሩ በእምነታቸው እስልምናን እየተቀበሉ የመጡ ኢትዮጵያዊ ጎሣዎችን ስለሱዳናዊነታቸው ስትሰብክና ሲታማልል ቆይታለች። ዕምነትን

የማስፋፍት ነፃነት መከበር ያለበት መሆኑን ብንቀበልም፣ ሃይማኖትን እንደፖለቲካ መሣሪያ መጠቀምን ግን በጥሞና ልናጤነው ያስፈልጋል። ሱዳን ወደ ደቡብ ሱዳንና ወደ ኢትዮጵያ ለመስፋፋት ሃይማኖትን ስትጠቀም ቆይታለች። እስልምናን ከመስበኩ ጋር አያይዛ በጥቅሉ ቤኒሻንጉል እየተባሉ በሚጠሩት ኢትዮጵያውያን መካከል ሱዳናዊነትን እንዲሰብኩ መልምላ ያሰማራቻቸው የፖለቲካ ካድሬዎች ነበሯት። በጭልጋ አውራጃ ከቋራ ጀምሮ እስከመተከል አውራጃ ምዕራባዊ ዳርቻና በወለጋ አሁን "ቤኒሻንጉል" አስተዳደር የተባለውን ክልል ጨምሮ፣ ዳርዳሩን እስከጋምቤላ ድረስ በሚገኙት ኢትዮጵያውያን ጎሣዎች ማለትም በጉምዞች፣ በሻንቅላዎች፣ በጉባዎች...ወዘተ መካከል ያልተቋረጠ የፖለቲካ ሥራ ስትሠራ ኖራለች።

ሱዳናውያን አሁን ኢትዮጵያን እየገዙ ያሉትን ነገር ግን ምንም የኢትዮጵያዊነት ዕምነትም ሆነ የሀገር ፍቅር ጠብታው እንኳን የሌላቸውን ጎሠኛና ጠባብ ብሔሬተኞችን አዲስ አበባ ላይ ለሥልጣን ካበቁበት ወቅት ጀምሮ፣ ያለምንም ጦርነት የወሰን መሬታችንን በእጃቸው ሊያስገቡ እንደሚችሉ ተስፋ አድርገው ነው የሚኖሩት። የህወሓት የመከላከያ ሚኒስቴር የነበረው ሰዬ አብርሃ ገና መጀመሪያ አንድ "የኢትዮጵያ ልዑክ ወደሱዳን እንደ ሄደ ነበር ሱዳኖች የወሰን መካለሉን ጥያቄ ያቀረቡልን፤ በዚያን ወቅትም ልዑኩ ለዚያ ዓይነት ድርድር እንዳልተዘጋጀ ነግረን ተመለስን" ብሎናል። በወቅቱ የሱዳን መንግሥት ጉዳዩን አቅልሎ ስላየውና መለስና ግብረ-አበሮቹም ለመስጠት ተባባሪ እንደሚሆኑ ተማምኖ ስለነበር ነው በጥድፊያ ማስፈጸም የተነሳሳው። እዚህ ላይ፣ መለስና ግብረ-አበሮቹ የሰነቀሩት አንቀጽ 39 ሌላ የሱዳን መሣሪያም ሊሆን እንደሚችል ማስተዋል አስፈላጊ ነው። የቤኒ ሻንጉል ክልል አንድ ማለዳ ተነስቶ እኔ እኮ "ሱዳናዊ" ነኝ ሊለንና ፀረ-ኢትዮጵያው የባንዳ ቡድን ባስቀመጠው ወጥመድ ገብቶና ተጠቅሞም እገነጠላለሁ ቢልስ? ከላይ እንደጠቀሰነው፣ ጉዳዩን በጥሞና ልናጤነው የሚገባ ነው።

ምናልባትም ለሱዳን ወዳጆቻቸው ሚስጥራዊ ቃል የሰጠው ሟቹ መለሰ ዜናዊና ጥቂት ሚስጥረኞቹ ብቻ ሊሆኑ ይችላሉ። ታዲያ ሰዬ አብርሃ ጉዳዩን ቀድሞ የሚያውቀው አይመስልም። ለማንኛውም ሱዳን አቅፋና ደግፋ ለፖለቲካ ሥልጣን ያበቃችው ቡድን በሰላም የምትፈልገውን የወሰን አካባቢ መሬታችንን ሊያስረክባት ዝግጁ እስከሆነላት ድረስ ለጊዜው አልተጨነቀችም። ለምንስ ብላ ሃሳብ ይግባት?! ይሄኔ እኮ ነው፣ "ሲፋጅ በማንኪያ ሲበርድ በጅ!!" የሚባለው። ሕዝብን መብት-አልባ በማድረግ አፍኖ፣ በዘር ከፋፍሎ፣ እርስ-በርስ አናቁሮ፣ ሀገራዊ ስሜቱን ከመጠን በላይ አዳክሞ፤ ቅስሙን ሰብሮና በተቃዋሚነት

የተሰለፉትን ሁሉ በተንኮልና በሠርጎ-ገቦች እየከፋፈለ አዳክሞ፣ አሁን በሌጣ ሊጋለበን፣ ሊገዛንና ሊነዳን መቻሉ ምን ይደንቃል? እንደማንኛውም አምባገነን ገዥ ሁሉ መለስን የተኩት ሳይቀሩ፣ ዛሬም ሀገራችንና መሬታችንን በቁጥጥራቸው ሥር አድርገው የፈለጉትን ለማድረግ እየዳዳቸው ነው። ስለዚህ ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ የሥልጣን ባለቤትነቱን፣ የሀገሩን ሉዑላዊነትና የዳርና ድንበሯን መከበር ጭምር ለማረጋገጥ ከዳር እስከዳር ተነሳስቶ ዘብ ሊቆም ይገባዋል! ይህ ብቻ አይበቃምና እነዚህን ሥልጣን ላይ ቁጢጥ ያሉትን የባዕድ ተጠሪዎችና አምባገነን ገዥዎች በቃችሁ ሊላቸው ይገባል! ሀገር ስትፈርስ፣ ድንበር ሲቆረስና የሀገር ክብር ሲነካ ዝም ብሎ መመልከት ከሀገር ክህደት ያልተናነሰ ምሕረት የማይደረግለት ጥፋት ነውና ሁላችንም የጉዳዩን አሳሳቢነት ተረድተን የዜግነት ግዴታችንን እንወጣ!

ሀገራችን ተሸራርፋ ሳታልቅ እንድረስላት!

በተጠናከረ የልጆቿ ትግልና መስዋዕትነት የኢትዮጵያችን ዳር ድንበር ተከብሮ ይኖራል!